**ማስጠንቀቅያ / ሱናሚ**

እውነታዎች: በዋሽንግተን ክፍለሃገር፡ በፓሲፊክ ውቅያኖስ ባህር ዳር በኩል፡ ለሚገኙ ክልሎች የሱናሚ ማስጠንቀቅያ ወጥቷል።ሱናሚ ማለት በውቅያኖስ መሬት ውስጥ ተከታታይ የመሬት መንቀጥቀጥ ሲያጋጥም የሚነሳ ሃይለኛ ተከታታይ ማዕበል ነው። ማንኛውም ማእበል፡ ኣነሰም ተለቀም፡ ከውሃ ጋር የተቀላቀሉ ሃይለኛ ነፋሶችን ኣስከትሎ፡ ከፍተኛ ጉዳት ሊያመጣና በቀላሉም ሰዎችን ከመሬት ሊያነሳ የሚችል ነው።

**ምን ማድረግ ያስፈልጋል:**

- በባህር ኣጠገብ የመሬት መንቀጥቀጥ ከተሰማዎት፡ በቅድሚያ ራስዎን ለመጠበቅ፡ ከጠረጴዛ ስር መግባት፡ ጠንከር ያለ የቤት ዕቃ ኣጠገብ በመጠጋት መከላከያ ማድረግ። በባህር ኣጠገብ ሱናሚ እንደሆነ የሚያመለክት የመጀመርያው ማስጠንቀቅያ የመሬት መንቀጥቀጥ ነው። የመሬት መንቀጥቀጡ ልክ ሲያቆም ተጣድፎ ከፍ ወዳለ መሬት መሮጥ ያስፈልጋል። ከፍታ ያለው መሬት ከሌለ ወይም ከፍ ወዳለው መሬት ለመድረስ ግዜ የማይበቃ ከሆነ፡ ወደ ከፍተኛ ፎቅ የመጨረሻ ደረጃ ላይ መውጣት።
- ቤትዎን እንዲለቁ ከታዘዙ ወድያውኑ ይልቀቁ። በቤት መልቀቅያ ማስታወቅያ ላይ ከሰፈሩት መንገዶች ውስጥ ኣንዱን ተከትለው ይሂዱ። ኣንዳንድ መንገዶች ኣትለፉ የሚሉ ምልክቶችና ጽሁፎች ሊደረግባቸው ይችላል።
- ቤትዎን ለቆ ለመውጣት መኪና መጠቀም ካልቻሉ፡ በእግሮ ይሂዱና ቅርብ የሆነ ከፍ ያለ መሬት ፈልገው በቀጥታ እዛ ይውጡ። ከሃይቆችና እርጥበት ካላቸው መሬቶች ራቁ። ምክንያቱም የመሬት መንቀጥቀጥ ካለፈ በውሃላ፡ በሚከተለው የመሬት መንከላወስ ጎርፍና የውሃ መጥለቅለቅ ሊያስከትሉ ይችላሉና።
- ኣደጋውን በሚመለከት ኣዲስ መረጃ እንዳለ ለማወቅ በቀጣይነት ሬድዮ ተከታተሉ ።
- ***ይህንን መልእክት ለመረዳት፡ ለማየትም ሆነ ለመስማት የማይችል  የሚያውቁት ሰው ካለ፡ እባክዎትን መልእክቱን ኣስረዷቸው።***

**ጠቃሚ ዌብሳይቶች:**

http://mil.wa.gov/emergency-management-division/hazards/tsunami

http://www.tsunamiready.noaa.gov/

http://www.ready.gov/tsunamis